Ministry of Housing,
Communities &
Local Government

**ኣሊስተይር ዎተርስ (Alistair Watters)**

*ዳይረክተር፣ የግረንፈል ግብያ እና መርሃ ግብር*

***የቤቶች፣ ማህበረሰቦች እና የአካባቢ መንግስታዊ ኣስተዳደር***

2 Marsham Street

London SW1P 4DF

3 ሐምሌ 2020

የተከበራችሁ፣

የምጽፍሎዎት በሀዘን እንዳሉ ቤተሰቦች እና የቀድሞ የግረንፈል ታወር ነዋሪ እንደመሆንዎ መጠን በቅርቡ ብህንጻው ስለሚከናወኑ የደህንነት ስራዎች ልነግርዎት ነው። እንደምታውቁት፣ መንግስት በሐምለ 2019 የግሬንፍሌል ታወር ባለቤትነትን ተረክበዋል፡፡ ለወደፊቱ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ደህንነቱ ኣስተማማኝነቱ የተጠበቀ የማድረግ እዲሁም ደግሞ ሕይወታቸውን ያጡ ሰዎችን ለማስታወስ ተገቢ ታሰቢያ የማድረግ ሃላፊነቱን ወስደናል።

እነዚህን አስፈላጊ ስራዎችን የሚገልጽ እና ለምን አሁን እየጀምርን እንዳለ የሚገልፅ የእውነታዎች ጽሑፍ (ፋክት ሺት) አካትቻለሁ፡ ፡ ስራዎቹ በመጪው ዓመት በመስከረም ወር የሚጀምሩ ሲሆኑ ደረጃ በደረጃ ይከናወናሉ፡፡ በአብዛኛው ደግሞ የሚከተሉትን የሚያካትት ነው፡

- ከዚህ ወር ጀምሮ፣ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ ይህ መሳሪያዎችቨ ወደ ቦታው ማድረስ እና ለመሳርያዎቹ ቦታ ለመፍጠር የጋራ ከሆኑ ቦታዎቹ አንዳንድ ትላልቅ እቃዎች መወገድን የመሳሰሉ ስራዎችን ያካትታል።

- ከመስከረም ወር ጀምሮ ከህንፃው ክብደትን ለመቀነስ ከባድ እና የተጎዱ እቃዎችን ማስወገድ፡፡ ይህም የተንጠለጠሉ ጣሪያዎችን እና ቧንቧዎችን ጨምሮ ሊመለሱ የማይችሉ እቃዎችን ከእያንዳንዱ የግል አፓርተማዎች የማጠብያ ገንዳዎች፣ ነጭ እቃዎች፣ የቤት እቃዎች እና መገጣጠሚያዎች መወገድን ያካትታል፡፡

- ክብደትን ለመቀነስ እንዲሁም የአከባቢው ነዋሪዎችን እና በህንፃው ውስጥ የሚሠሩትን ቀጣይ ደህንነት ለማረጋገጥ - ከነልግ ወቅት ጀምሮ ኣስቤስቶስን መወገድ፡፡ በመላው የማስወገድ ሂደት የሕዝቡን ደኅንነት ለማረጋገጥ ከልዩ ባለሙያ ሎንትራክተር ጋር እየሰራን ነው፡፡

- ከዚህ በኋላ ፣ እዚያ ለነበሩት ላይ ተጨማሪ እንዲሆን እና ለወደፊቱ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ እና የህንጻው መረጋጋት ለማረጋገጥ ኣዳዲስ መደገፊያች መትከል።

- እነዚህ ስራዎች ስሜትን የሚነኩ መሆናቸውን እረዳለሁ እናም ይህ ለምን እየተከናወኑ እንደሆኑ ግልጽ መሆን እፈልጋለሁ፣ ጥያቄዎችዎን ለመመለስ እና ስለእነሱ ሊኖርዎት የሚችለውን ማንኛውንም ስጋቶች መስማት እፈልጋለሁ፡ ፡ የሚከተለውን ኣጽንቼ መንገር እፈልጋለሁ፡

- ህንጻው ኣስተማማኝ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ነው። ለወደፊቱ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ እነኚህ አስፈላጊ የሆኑ ስራዎች የሚሰሩት ቀጣይ መረጋጋትን ለማረጋገጥ ናቸው ፡፡ ውሳኔው የሚሰጥው ከአካባቢው ማህበረሰብ እና ከግል ባለሞያዎች ጋር በቅርብ በሚደረግ ውይይት ብቻ ነው፡፡

- ከእሳቱ በኋላ በነበሩት ወራቶች ገለልተኛው የጣቢያው የአስተዳደር ቡድኑ ለቀድሞ ነዋሪዎቹ ሊመለሱ የሚችሉ፣ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ ወይም ዓላማ ያላቸው ተደርገው የሚቆጠሩትን የግል እቃዎች ለማስወገድ እና ለመመለስ ከልዩ ባለሙያተኛ ኮንትራክተር ጋር አብረው ሰርተዋል፡፡ ያ ሂደት አሁን ተጠናቅቋል።

- እነዚህ ስራዎች በፍትህ እና በተጠያቂነት ሂደት ላይ ጣልቃ አይገቡም፡፡ የፎረንሲክ ሃኪም፣ ፖሊስና የግሬንፍል ታወር ምርመራው ሁሉም ከህንጻው የሚፈልጉትን ማስረጃ እንዳላቸውና ለጀመሩ ስራዎችም እርካታ እንዳላቸው አረጋግጠዋል፡፡

- ለወደፊቱ መታሰቢያ የሚሆኑ ሀሳቦች እና እቅዶች ማዘጋጀት በገለልተኛ የመታሰቢያ ኮሚሽን ይመራሉ ፡፡ ከነሱ ጋር ለመገናኘት እና የሚሰጡዋቸው ኣዳዲስ መርጃዎችን ለማግኘት ብድረጹ፡ www.grenfelltowermemorial.co.uk መመዝገብ ይችላሉ።

**የግሬንፈል ታወር ኣስተዳደር** በሚከተለው ጉዳይ መረጃ ለስጠት ሃዘን ከደረሰባቸው ቤተሰቦች ወይም ከቀድሞ ነዋሪዎች ጋር **የግል ውይይት ለማድረግ ዝግጁ** ነው፡
እነዚህ ስራዎች በግል ኣፓርታማዎች ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ከእነሱ ጋር ለመገናኘት፡
ኢመይል በመላክ GTMCSecretariat@communities.gov.uk ወይም ተሌፎን 0303 444 0011 በተጨማሪም ለዚህ ተብለው የተወሰኑ አገልግሎት እና የአከባቢ የጤና አገልግሎቶች እነዚህ ስራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን እንዲገነዘቡ አድርገናል እናም ጥያቄ ካለዎት እኛን ለማግኘት እኛን ይረዱዎታል፡፡

ከመልካም ምኞት ጋር



ኣሊስተይር ዎተርስ (Alistair Watters)